# የ አየርላንድ የዓለም አቀፍ ጥበቃ አሰራር መመሪያ




www.unhcr.ie

UNHCR
The UN Refugee Agency

# ስለ እኛ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን ቢሮ ከሃገራቸው ለመሰደድ ለተገደዱ ሰዎች ጥበቃ ለማድረግ እና በሌሎች ሃገራት ውስጥ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ ኃላፊነት የተሰጠው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ነው። የአየርላንድ የUNHCR አገራዊ ቢሮ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቶች ሥልጠና እና ድጋፍ በመስጠት እንዲሁም በሕግ፣ በፖሊሲ እና አሰራሮች ውስጥ ምርጥ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን በማስተዋወቅ አየርላንድ ውስጥ የሚገኙ ስደተኞችን፣ ጥገኝነት ጠያቂዎችን እና ዜግነት የሌላቸውን ሰዎች መብት ለማስጠበቅ ይሰራል። በተወሰኑ አጋጣሚዎችም ለግለሰብ ስደተኞች፣ ጥገኝነት ጠያቂዎች እና ዜግነት የሌላቸው ሰዎች እገዛ፣ ድጋፍ ወይም ምክር እንሰጣለን።

እ.ኤ.አ ዲሴምበር 2016 ላይ **የዓለም አቀፍ ጥበቃ ሕግ 2015** በመባል የሚጠራው ሕግ አየርላንድ ውስጥ በስራ ላይ ውሏል። አየርላንድ ውስጥ የዓለም አቀፍ ጥበቃ አፈጻጸምን ለመመርመር አዲስ ነጠላ የጥበቃ አሰራር ያስቀምጣል። ይህ የመረጃ መጽሃፍ በአዲሱ ሕግ መሰረት የተደረጉትን ዋና ዋና ለውጦች እና አዲሱን የጥገኝነት ጥያቄ ሂደት በተመለከተ አጠቃላይ መግለጫ ያቀርባል እንዲሁም አየርላንድ ውስጥ ዓለም አቀፍ ጥበቃ የሚፈልጉ ሰዎችን እና ጥገኝነት ጠያቂ ሰዎችን ጉዳይ የሚያከናውኑ ሰዎችን ያግዛል።.[1]

# ውሳኔ ሰጪ አካላት

እነዚህ የእርስዎን የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ የሚመረምሩ ድርጅቶች ናቸው።

### የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ (The International Protection Office, IPO)

የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ፣ በአየርላንድ የዜግነትና የፍልሰት አገልግሎት (Irish Naturalisation and Immigration Service, INIS) ውስጥ የሚገኝ ቢሮ ሲሆን ኃላፊነቱም የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎችን መመርመር ነው። በዓለም አቀፍ ጥበቃ ላይ ውሳኔ የሚሰጡ የስራ መኮንኖች ገለልተኝነት በአየርላንድ ሕግ ጥበቃ ይደረግለታል። አየርላንድ ውስጥ ከመግቢያ ወደብ ሌላ ባለ ቦታ ላይ ጥገኝነት ለመጠየቅ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ዘንድ በአካል በመቅረብ ማመልከት ያስፈልግዎታል። ይህ ቢሮ በ2017 መጀመሪያ ላይ የስደተኞች ማመልከቻ ኮሚሽነር ቢሮን (ORAC) ተክቷል። የበለጠ ለማወቅ እባክዎ ይህንን ድረ ገጽ ይጎብኙ:- www.ipo.gov.ie

### የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት( The International Protection Appeals Tribunal, IPAT)

የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት(IPAT) ገለልተኛ ጉባዔ ነው። IPO ዓለም አቀፍ ጥበቃ (የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ንዑስ-ጥበቃ) ሊያገኙ አይገባም በሚል ምክረ ሃሳብ የሰጠባቸውን ሰዎች ይግባኞች ይመረምራል። ይህ ቢሮ በ2017 መጀመሪያ ላይ የስደተኞች ይግባኝ ጉባዔን ተክቷል። የበለጠ ለማወቅ እባክዎ ይህንን ድረ ገጽ ይጎብኙ:- www.protectionappeals.ie

[1] **የክህደት ቃል** ይህ የመረጃ መጽሃፍ ለመረጃ ዓላማ ብቻ የተዘጋጀ ሲሆን የሕግ ምክርን የያዘ አይደለም እንዲሁም ሊለወጥ የሚችል ነው። ለበለጠ መረጃ እባክዎ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች የተዘጋጀውን የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ መረጃ መጸሀፍ www.ipo.gov.ie ላይ ይመልከቱ።


# 1 ነጠላ አሰራር

በ2015ቱ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ሕግ አማካኝነት ከተዋወቁት ለውጦች መካከል በጣም ወሳኙ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎችን ለመመርመር በስራ ላይ የዋለው አዲስ ነጠላ አሰራር ነው። ይህም ማለት የስደተኝነት ሁኔታ፣ ንዑስ ጥበቃ እና የመቆየት ፈቃድ በአንድ ላይ በተመሳሳይ ሂደት ውስጥ ይመረመራሉ ማለት ነው። ይህም በጥገኝነት ጥያቄ አሰራር ላይ የሚፈጠሩ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆዩ መዘግየቶችን ያስቀራል።




# 2 የማመልከቻ ሂደቱ

ይህ ስዕላዊ መግለጫ ስለ አየርላንድ አዲሱ የማመልከቻ ሂደት አጠቃላይ መግለጫ የሚሰጥ ሲሆን በእያንዳንዱ ደረጃ ከታች ከሚገኘው ጽሁፍ ጋር በጋራ መነበብ አለበት። ከዚህ የመረጃ በራሪ ወረቀት ጀርባ በይበልጥ በዝርዝር የተቀመጠ ፍሎው ቻርት ይገኛል።



## ደረጃ 1 ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት

በግዛቱ ድንበር ላይ ወይም በግዛቱ ውስጥ IPO በመገኘት ዓለም አቀፍ ጥበቃ መጠየቅ ይችላሉ። ራስዎን ወክለው እና/ወይም ከ18 ዓመት በታች ያሉና በርስዎ ጥገኝነት ስር ያሉ ልጆችዎን ወክለው ዓለም አቀፍ ጥበቃ መጠየቅ ይችላሉ። ልጆችዎ የአየርላንድ ዜግነት ያላቸው ካልሆነ በስተቀር በግዛቱ ውስጥ እያሉ ከተወለዱ ወይም እርስዎ በጥበቃ አሰራር ውስጥ እያሉ ከገቡ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በእርስዎ አቤቱታ ውስጥ ጥገኞችዎ ሆነው ይካተታሉ። ልጆች ያለዎት አመልካች እንደመሆንዎ፣ በአሰራሩ ወቅት ከልጆችዎም ሆነ ከእርስዎ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም አሳሳቢ ጉዳዮች ማንሳትዎ በጣም ወሳኝ ነው።

**ተስላ የተሰኘው የልጆች እና የቤተሰብ ድርጅት፣** በእነርሱ ጥበቃ ውስጥ ላሉና ወላጅ አብሯቸው ለሌለ ልጆች ዓለም አቀፍ ጥበቃ ይጠይቃሉ።

## ደረጃ 2 የመጀመሪያ ደረጃ ቃለ-መጠይቅ

አየር ማረፊያ ወይም የባህር ወደብን በመሳሰሉ በግዛቱ ድንበሮች ላይ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ከጠየቁ፣ የፍልሰት ስራ መኮንን እና/ወይም የ IPO ስራ መኮንን ቃለ-መጠይቅ ያደርጉልዎታል። ይህም ማንነትዎን፣ የመጡበትን ሃገር፣ ወደ አየርላንድ ለመምጣት የተጓዙበትን የጉዞ መስመር እና ዓለም አቀፍ ጥበቃ የሚጠይቁባቸውን አጠቃላይ መሰረቶችን የመሳሰሉ ለመነሻ የሚሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ነው። ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ቃለ-መጠየቅ በድንበሮቹ ላይ ካልተከናወነ፣ በ IPO ቢሮ ውስጥ ይከናወናል።

በተጨማሪም የመጀመሪያ ደረጃ ቃለ-መጠይቁ ማመልከቻዎ ተቀባይነት ያለው መሆኑንም ይመረምራል። ይህም ማለት አየርላንድ ውስጥ ጥገኝነት ለመጠየቅ ማመልከቻ ለማቅረብ የሚችሉ መሆን አለመሆንዎን የ IPO የስራ መኮንን ይወስናል ማለት ነው። በሌላ የአውሮፓ ህብረት አባል ሃገር ውስጥ የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ንዑስ- ጥበቃ ተሰጥቶዎት የነበረ ከሆነ ወይም ከአውሮፓ ህብረት ውጪ ያለ የስደተኝነት ሁኔታ ሰጥቶዎት የነበረ እና ጥበቃ ሊያገኙበት ወደሚችሉበት ቦታ ሊመልስዎት ፈቃደኛ የሆነ ሃገር ካለ ይህንን ለማድረግ አይችሉም።

**ማመልከቻዬ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነስ ምን ይፈጠራል?**
ለ የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ይግባኝ ለማቅረብ የሚችሉበትን የጊዜ ገደብ ጨምሮ ከ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ ይደርስዎታል። ለየአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት የሚቀርበው ይግባኝ በጽሁፍ ብቻ ይሆናል።

የመጀመሪያ ደረጃ ቃለ-መጠይቅ የተደረገልዎት በግዛቱ ድንበሮች ላይ ከሆነ፣ ከዚያ በመቀጠል ወደ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ግቢ ይመራሉ። የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ውስጥ የእርስዎ እና በርስዎ ጥገኝነት ስር ያሉ ሰዎች አሻራ ይነሳል እንዲሁም ፎቶግራፍ ትነሳላችሁ። ይህ መረጃ የሚወሰደው ማንነትዎን ለማረጋገጥ እና በርስዎ ጉዳይ ላይ የደብሊን ደንብ ተፈጻሚ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ነው።

በማስከተልም የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎን ለመከታተል በአየርላንድ ውስጥ እንዲቆዩ የተፈቀደልዎት መሆኑን የሚያመለክት ጊዜያዊ የመኖሪያ ምስክር ወረቀት ይሰጥዎታል። መደበኛ መታወቂያ ካርድ አይደለም፤ ነገር ግን በማንኛውም ጊዜ ሊይዙት ይገባል። በጥበቃ አሰራር ሂደት ውስጥ እያሉ ሊታደስ ይችላል።

# ደረጃ 3 መጠይቅ

የ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የስራ መኮንን የሆነ ሰው ነጠላ አሰራሩን የሚመለከት የመረጃ መጽሃፍ እና ሞልተው ለ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ  የሚመልሱት መጠይቅ ይሰጥዎታል። የመረጃ መጽሃፍ መጠይቁን ከመሙላትዎ እና ሕጋዊ እገዛ ከመጠየቅዎ በፊት መሙላትዎ በጣም ወሳኝ ነው።

መጠይቁን ሙሉ በሙሉ መሙላትዎ እና የዓለም አቀፍ ጥበቃ ፍላጎቶችዎን የሚመለከቱ ትክክለኛ መረጃዎችን መስጠትዎ ወሳኝ ነገር ነው። ያልተረዷቸው የመጠይቁ ክፍሎች ካሉ፣ የአማካሪዎን እርዳታ ይጠይቁ።

የሚቻል ከሆነ፣ መጠይቁ በ20 የስራ ቀናት ውስጥ ማለትም በ4 ሳምንታት ውስጥ መመለስ አለበት። ይህም አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ማመልከቻዎችን በተቻለ መጠን በቅልጥፍና እንዲያስተናግድ ለማገዝ ነው። መጠይቁን ለመሙላት ወይም የሕግ አማካሪ ለማማከር ተጨማሪ ጊዜ የሚፈልጉ ከሆነ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሁኔታዎች ሊመቻቹ እንደሚችል ለአመልካቾች ማረጋገጫ ይሰጣል።  ይህ እርስዎን የሚመለከት ከሆነ አማካሪዎን ያነጋግሩ ወይም በቀጥታ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ን በማነጋገር ያሳውቁ (የአድራሻ መረጃን በተመለከተ ገጽ 21ን ይመልከቱ)።

በተጨማሪም ለማመልከቻዎ አግባብነት ይኖራቸዋል ብለው የሚያስቧቸውን ማናቸውንም ደጋፊ ሰነዶች ማቅረብዎ አስፈላጊ ነው። ይህ የመቆየት ፈቃድ ከሚቀርብ ማመልከቻዎ ጋር የተያያዙ መረጃዎችንም ያካትታል።

# ደረጃ 4  ግላዊ ቃለ-መጠይቅ

አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ለቃለ-መጠይቅዎ የቀጠሮ ደብዳቤ ይልክልዎታል። አስፈላጊ ከሆነ፣ አስተርጓሚ  ይዘጋጅልዎታል። መጠይቅዎን ካስረከቡ በኋላ ያገኙት ተጨማሪ መረጃ እና/ወይም ማስረጃ ካለዎት ይህንን መረጃ ቃለ-መጠይቅዎ እንዲከናወን ከተቀጠረበት ቀን ቢያንስ ሁለት ሳምንት ቀድመው ያስገቡ።
ቃለ-መጠይቁ አየርላንድ ውስጥ ጥበቃ እንዲደረግልዎ ለምን እንደጠየቁ ምክንያቶችዎን በሙሉ የሚያቀርቡበት ዕድል ነው።   በቃለ-መጠይቁ እለት እርስዎ እና አስተርጓሚዎ እርስ በርስ መግባባታችሁን ያረጋግጡ።

አስተርጓሚዎን ለመረዳት ከተቸገሩ፣ እባክዎ ይህንን ለ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የስራ መኮንን ያሳውቁ። የ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የስራ መኮንኑ አስቀድሞ የሞሉትን መጠይቅ አንብቦ ስለሚሆን ስለጉዳይዎ ያውቃል። የ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የስራ መኮንኑ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች ለመረዳት ከተቸገሩ፣ እባክዎ ጥያቄዎቹን እንዲደግምልዎት ይጠይቁ። ከመቆየት ፈቃድ ውሳኔ ጋር በተያያዘ ሚኒስትሩ ሪፖርት እስከሚያዘጋጅበት ጊዜ ድረስ ለመቆየት ፈቃድ ለሚቀርብ ማመልከቻዎ አግባብነት ያላቸውን ማናቸውንም የሁኔታ ለውጦች በተመለከተ ለሚኒስትሩ የማሳወቅ ግዴታ ያለብዎ መሆኑን ያስታውሱ።

የአቤቱታዎን የመቆየት ፈቃድ ገጽታ በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ለመስጠት ከፈለጉ፣ ይህንን ለማድረግ ያለዎት ዕድል ይሄ ነው። የቃለ-መጠይቅዎን ቀን ጨምሮ እና እስከ ቃለ-መጠይቅዎ ቀን ድረስ ማመልከቻዎን በተመለከተ እርስዎ ወይም አማካሪዎ በጽሁፍ መረጃ መስጠት ይችላሉ።


ቃለ-መጠይቁ በጽሁፍ ተመዝግቦ ከ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ስራ መኮንኑ ዘንድ ይቀመጣል።  በቃለ-መጠይቁ ወቅት፣ በየተወሰኑ ጊዜያት ቃለ-መጠይቅ አድራጊው ያቋርጥዎትና በተናገሩት ነገር ላይ ማንኛውንም አይነት ማብራሪያ ወይም እርማት ለመስጠት አስፈላጊ ከሆነ የያዘውን ማስታወሻ ይከልሳል።  ከዚያም ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ በተመዘገበው ቃለ-መጠይቅ ላይ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ።  በተመዘገበው ቃለ-መጠይቅ ላይ ማንኛውም ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ከተገኘ፣ ወይም የታለፈ ነገር ካለ፣ ለማብራራት ይችሉ ዘንድ በቀጥታ ለቃለ-መጠይቅ የስራ መኮንኑ ያሳውቁት።

ምንም እንኳን የተለመደ አሰራር ባይሆንም አማካሪዎ በቃለ-መጠይቁ ላይ ሊገኙ ይችላሉ። ቃለ-መጠይቁ ከመጀመሩ አስቀድሞም እርሱ/እርሷ እርስዎን ወክለው መግለጫ ሊሰጡ ይችላሉ። ወላጅ አብሮህ/ሽ የሌለ ህጻን ልጅ ከሆንሽ/ክ ከተስላ የመጣ ሞግዚት ወይም ወኪል በቃለ-መጠይቁ ላይ የግድ መገኘት አለበት። ቃለ-መጠይቁ ባልተጠበቁ ሁኔታዎች ጊዜ ብቻ ሊራዘም ይችላል፤ ለምሳሌ በሕመም እየተሰቃዩ ከሆኑ። ቀጠሮ በተያዘበት ቀን በቃለ-መጠይቁ ላይ ለመገኘት የማይችሉ ከሆነ፣ ወዲያውኑ ለ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ማሳወቅዎ ጠቃሚ ነው። ቃለ-መጠይቁ በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ብቻ ሊሰራጭ ይችላል።.[2]

## ደረጃ 5 የ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ውሳኔ

ቃለ-መጠይቁን ተከትሎ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ጉዳይዎን የሚመለከቱ አግባብ የሆኑ መረጃዎችን በሙሉ ያጤናል። ይህም የተመዘገበውን ቃለ-መጠይቅ እና የተሞላውን መጠይቅ ያካትታል። በስድስት ወራት ውስጥ ምክረ ሃሳብ ካልተሰጠ፣ ከ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ውሳኔ ሊያገኙበት የሚችሉበትን የጊዜ ግምት በተመለከተ መረጃ መጠየቅ ይችላሉ።

የምክረ ሃሳቡ ውጤት ሊሆኑ የሚችሉ ሃሳቦች ዝርዝር ከዚህ በታች በሚገኘው ሠንጠረዥ ውስጥ ተመልክቷል። ምክረ ሃሳቡ፣ በግለሰብ ደረጃ ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ የተሰጠው ምክረ ሃሳብ ላይ ሊደረስ የተቻለባቸውን ምክንያቶች ሃተታ ያካትታል። በምክረ ሃሳቡ ውስጥ የሚገኙት የተወሰኑ ግኝቶች ለማንኛውም ይግባኝ የሚሰጠውን የጊዜ ገደብ እና የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ዘንድ በቃል የመሰማት ሂደት መፈቀድ አለመፈቀዱን ይወስናሉ።




[2] ለበለጠ መረጃ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች የተዘጋጀውን የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የመረጃ መጽሃፍ ክፍል 4.5.12 ይመልከቱ።

ምክረ ሃሳቡ ለእርስዎ እና/ወይም ለአማካሪዎ በተመዘገበ የመልዕክት ጥቅል ይደርስዎታል። አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የስደተኝነት ሁኔታ ሊሰጥዎ ይገባል የሚል ምክረ ሃሳብ ካቀረበ የፍትሕ እና እኩልነት ሚኒስትር (ሚኒስትሩ) በበርካታ ሳምንታት ውስጥ የስደተኝነት ማሳወቂያ ይሰጥዎታል። በጣም ውስን በሆኑ አጋጣሚዎች አመልካቹ ለደህንነት ስጋት ነው ተብሎ ከታመነ ሚኒስትሩ የ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮን ምክረ ሃሳብ ለመከተል ሊቃወም ይችላል።

የስደተኝነት ሁኔታ ከተከለከሉ ነገር ግን ንዑስ ጥበቃ ከተፈቀደልዎት፣ ለስደተኝነት ሁኔታ የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ዘንድ ይግባኝ ለማቅረብ አሁንም መብት ይኖርዎታል። የስደተኝነት ሁኔታም ንም ሆነ ንዑስ ጥበቃም ከተከለከሉ ሚኒስትሩ "የመቆየት ፈቃድ" ይሰጥዎት ወይስ አይሰጥዎት በሚለው ላይ ይወስናል። ውሳኔው የመቆየት ፈቃድ የሚሰጥዎ ይሁንም አይሁን፣ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ማግኘትዎን በሚቃወመው ውሳኔ ላይ ለ የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።

የስደተኝነት እና/ወይም የንዑስ ጥበቃ ሁኔታ ካልተፈቀደልዎት፣ የተመዘገበው ቃለ-መጠይቅ ቅጂ እና ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኞች ጉባዔ ይግባኝ የማቅረብ መብትዎን የሚመለከት መግለጫ ይደርስዎታል። ሊከተሉት የሚገባውን ቅደም ተከተል የሚመለከት መረጃ እና ይግባኝ ለማቅረብ የሚሆን የይግባኝ ቅጽም እንዲሁ ይደርስዎታል። ማመልከቻዎ ሊያስገኛቸው የሚችሉትን ውጤቶች በተመለከተ ይበልጥ ዝርዝር የሆነ ፍሎው ቻርት ለማግኘት የዚህን በራሪ ወረቀት የጀርባ ገጽ ይመልከቱ።

## ደረጃ 6 ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኞች ጉባዔ የሚቀርብ ማመልከቻ

የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ንዑስ ጥበቃ ለማግኘት መብት የለዎትም በማለት በተሰጠ የ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ምክረ ሃሳብ ላይ የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ዘንድ በመቅረብ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። የመቆየት ፈቃድ አልተሰጠም በሚል ግን ለ የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም።

አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ በሚሰጥዎት የምክረ ሃሳብ ደብዳቤ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የይግባኝ ቅጽ ተሞልቶ ለየአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት መቅረብ አለበት። በ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ምክረ ሃሳብ ደብዳቤ ላይ በተቀመጡት ግኝቶች መሰረት ይግባኙ በቃል እንዲሰማ ሊጠይቁ ይችላሉ።

ይግባኝዎ የሚሰማበት ቀን ሲወሰን እርስዎ እንዲያውቁ ይደረጋል። ይግባኙ በሚሰማበት ቀን አስተርጓሚ የሚያስፈልግ ከሆነ እባክዎ እርስዎ እና አስተርጓሚው እርስ በርስ የምትግባቡ መሆኑን ያረጋግጡ። አስተርጓሚውን ለመረዳት ከተቸገሩ ይህንን ለጉባዔው አባል ያሳውቁ። በቃል መስማት ሂደቱ ላይ ከእርስዎ፣ ከአማካሪዎ እና ከጉባዔው አባል በተጨማሪ የ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ አባል ይገኛል። የጉባዔው አባል የጥበቃ ማመልከቻዎን አንዳንድ ገጽታዎች በሚመለከት ከጉባዔው ፊት ማስረጃ እንዲሰጥ ምስክር እንዲገኝ ሊያዝ ይችላል።

አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የሰጠውን አሉታዊ ምክረ ሃሳብ የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ከሻረው፣ ሚኒስትሩ አግባብ የሆነውን ጥበቃ ይሰጥዎታል ማለትም የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ንዑስ ጥበቃ።

**ከ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የመቆየት ፈቃድ ተሰጥቶኝ የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ንዑስ ጥበቃ በሚከለክለው ምክረ ሃሳብ ላይ ይግባኝ መጠየቅ ከፈለግኩስ?**

የመቆየት ፈቃድ ከተሰጠዎ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ማግኘትዎን በሚቃወመው የ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። እንዲሁም በአካባቢዎ በሚገኝ የፍልሰት ምዝገባ ቢሮ የመቆየት ፈቃድዎን ማስመዝገብ ይችላሉ።

# ደረጃ 7 የመቆየት ፈቃድ ክለሳ

ሚኒስትሩ የመቆየት ፈቃድ ካልሰጠዎት፣ እና ለየአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ያቀረቡት ይግባኝ ካልተሳካ፣ ሚኒስትሩ በማስከተል የመቅረት ፈቃድ እንዳይፈቀድልዎት የተሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ ዋናው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ያቀረቡት አዲስ መረጃ ካለ እርሱን ይከልሳል። የመቆየት ፈቃድ ክለሳ ቅጽ እንዲሞሉ ይሰጥዎታል። አዲስ መረጃ ለማስረከብ **5 የስራ ቀናት** ብቻ ይኖርዎታል ስለዚህ ለማቅረብ የሚፈልጓቸው ማናቸውም ሰነዶች ካሉ አስቀድመው ማግኘትዎን እርግጠኛ ይሁኑ። የሚኒስትሩ የመጀመሪያ የመቆየት ፈቃድ ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ እና የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት በይግባኝዎ ላይ ውሳኔ በሰጠበት ጊዜ መካከል ሁኔታዎች ከተለወጡ እና ለመቆየት ፈቃድ ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ ፈቃድዎን ለመከለስ አግባብ የሆኑ አዳዲስ መረጃዎች ካሉዎት በተቻለዎ ፍጥነት ለሚኒስትሩ ማሳወቅ አለብዎ።

የመቆየት ፈቃድ መከልከል ለእስራት ሊጋለጡ ወደሚችሉበት ሃገር ባለመላክ ላይ ያለውን ክልከላ የሚጥስ ከሆነ ሚኒስትሩ ይህንን ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል (ለበለጠ መረጃ፣ ከዚህ በታች **7ን ይመልከቱ። በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች**)።

# 3 የአመልካቾች መብትና ግዴታዎች

## ያሉኝ መብቶች ምን ምንድናቸው?

### የእርስዎ መብቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

የዓለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ከሆኑ መብቶችዎ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎን እስከሚመረምር እና ለየአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ለሚቀርብ ማንኛውም ማመልከቻ አየርላንድ መግባት እና እዚያው መቆየት
- ከጠበቃ የህግ ምክር የማግኘት እና የመወከል መብት
- በነጠላ አሰራሩ ሂደት በሙሉ በአክብሮት፣ በክብር እና በፍትሃዊነት መስተናገድ
- ከጥበቃ ማመልከቻዎ ጋር በተያያዘ ለሚኒስትሩ በጽሁፍ መረጃ ማቅረብ
- ተግባቦትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሲሆን አስተርጓሚ መጠቀም
- የሚስጥራዊነት መብት
- ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ካቀረቡት ማመልከቻ ጋር በተያያዘ ለሚኖሩ ማናቸውም ቃለ-መጠይቆች፣ ውሳኔዎች ወይም ሌሎች አግባብ የሆኑ ማስታወቂያዎች ላይ ማሳወቂያ የማግኘት መብት
- ከUNHCR ጋር የመገናኘት መብት

**ከሕግ ድጋፍ ቦርድ (LAB)** የሕግ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። እነርሱ ዘንድ ካሉ አማካሪዎች አንዱን ወይም ከእነርሱ ጋር የሚሰራ የግል አማካሪ ሊያዘጋጁልዎት ይችላሉ። LAB ለሁሉም የዓለም አቀፍ ጥበቃ ደንበኞች በማመልከቻቸው ገጽታዎች ላይ በሙሉ ከመጀመሪያው ደረጃ አንስቶ የሕግ ምክር ለመስጠት ቁርጠኛ ነው። ይህም መጠይቅዎን ሞልተው ከመጨረስዎ በፊት የሚከናወን የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምክክርን እና በሞሉት መጠይቅ መሰረት በአቤቱታዎ ክፍሎች ላይ የሚሰጥ የቅድመ-ቃለ-መጠይቅ ምክክርን ይጨምራል። **የአየርላንድ የስደተኞች ምክር ቤት ገለልተኛ የሕግ ማዕከል** እንደሚኖረው አቅም የመጀመሪያ ደረጃ የሕግ ምክር ይሰጣል። ገንዘቡ ካለዎት ከግል ጠበቃም አገልግሎቶቹን መጠየቅ ይችላሉ።

በማመልከቻዎ ልዩ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ በቃለ-መጠይቅዎ ወይም በይግባኝ መስማት ሂደት ላይ አንደኛው ጾታ ያለው አስተርጓሚ እንዲገኝ ሊመርጡ ይችላሉ። የሚቻል ከሆነ ይህንን ጥያቄዎን ለመቀበል እንዲችሉ በ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ እና/ወይም የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ዘንድ በተቻለ መጠን ጉዳዩን በጊዜ ማንሳትዎ ጠቃሚ ነው።

ከማመልከቻዎ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ማስረጃዎች በሙሉ በሚስጥር ይያዛሉ እንዲሁም በመጡበት ሃገር/አዘውትረው በሚኖሩበት ሃገር ውስጥ ላሉ ባለስልጣናትም ሆነ አየርላንድ ውስጥ ላሉ የሃገርዎ ተወካዮች አይገለጽም።

# ያሉብኝ ግዴታዎች ምን ምንድናቸው?

### የእርስዎ ግዴታዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- በአየርላንድ ውስጥ ላሉ ሕጎች መገዛት

ይህም ማለት የአየርላንድን ሕጎች እና ደንቦች ማክበር አለብዎት ማለት ነው።

- የመተባበር ግዴታ

በነጠላ አሰራር ውስጥ ያለ አመልካች እንደመሆንዎ በጥበቃ ማመልከቻዎ ምርመራ እና ከማመልከቻዎ ጋር በተያያዘ ለሚቀርብ ማንኛውም የይግባኝ ውሳኔ የመተባበር ግዴታ አለብዎ። ማመልከቻዎን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በሙሉ በምክንያታዊነት ተግባራዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስረከብ እና እውነተኛነቱን ማረጋገጥ አለብዎ። አለመተባበር በጥበቃ ማመልከቻዎ ውጤት ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ይኖራል።

### የአሰራር ግዴታዎች

የመተባበር ግዴታ ክፍል የሚከተሉትን ግዴታዎች ይጨምራል፡-

ሀ. የነጠላ አሰራሩ እየተካሄደ ባለበት ወቅት ከሚኒስትሩ ፈቃድ ውጪ አየርላንድን ለቆ አለመሄድ ወይም ለቆ ለመሄድ አለሞከር፤

ለ. በተቻለ መጠን አድራሻዎን እና ማንኛውንም የአድራሻ ለውጥ ለሚኒስትሩ በጽሁፍ ማሳወቅ፤

ሐ. አየርላንድ ውስጥ በተወሰነ ቦታ ላይ እንዲኖሩ እና/ወይም በየተወሰነ ጊዜ ለፍልሰት የስራ መኮንን ወይም በተገለጸ የጋርዳ (ፖሊስ) ጣቢያ ውስጥ በመገኘት ሪፖት እንዲያደርጉ ለሚወስኑብዎት ሪፖርት የማቅረብ ማስታወቂያዎች መገዛት፤

መ. ስምዎን፣ አድራሻዎን፣ ዜግነትዎን እና በጊዜያዊ የመኖሪያ ምስክር ወረቀትዎ ላይ የሚገኘውን የግል መታወቂያ ቁጥርዎን ከ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ወይም የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ጋር በሚያደርጉት ማንኛውም የመረጃ ልውውጥ ላይ ማመልከት፤

ሠ. ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ከሚያቀርቡት ማመልከቻ ጋር በተያያዘ እውነተኛ መሆን እና መጠይቁን ማመልከቻዎን ለመመርመር አግባብ በሆኑ መረጃዎች መሙላት፤

ረ. ከ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ እና የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት የተሰጡዎትን እና እርስዎም ለእነዚህ ድርጅቶች የሰጧቸውን ሰነዶች በሙሉ ቅጂ ማስቀመጥ።

## ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ያቀረብኩት ማመልከቻ በመመርመር ላይ እያለ ሥራ መስራት እችላለሁ?

ለጥበቃ ባቀረቡት ማመልከቻ ላይ ከዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ በ 6 ወራት ውስጥ ውሳኔ ካላገኙ፣ እንዲሁም መዘግየቱ የተከሰተው በእርስዎ ምክንያት ካልሆነ፣ ሥራ ለመስራት ፈቃድ እንዲሰጥዎ ሊያመለክቱ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ ይህንን ድረ ገጽ ይመልከቱ፡- www.inis.gov.ie

# 4 ሌሎች አግባብ የሆኑ መረጃዎች

### ቅድሚያ አሰጣጥ

የተወሰኑ የማመልከቻ ዓይነቶች በ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። ይህም ማለት እንደዚህ ዓይነት ማመልከቻዎች በተቻለ ፍጥነት ለቃለ-መጠይቅ ይቀጠራሉ። ይህ በእነዚህ ሁኔታዎች መሰረት የሚሰጥ ውሳኔን በቅድሚያ አይወስንም ወይም በእነዚህ ሁኔታዎች ወቅት ውሳኔ መቼ እንደሚሰጥ ማናቸውንም ተጨማሪ ዋስትናዎች አይሰጥም።

በተወሰኑ ምክንያቶች የተነሳ የእርስዎ ጉዳይ ቅድሚያ ሊሰጠው ይችላል፣ ይህም ከ70 ዓመት ዕድሜ በላይ ከሆኑ፣ ወላጅ አብሮት/ሯት የሌላ ህጻን ከሆንሽ/ክ፣ አሳሳቢ በሆነ የጤና ምክንያት ወይም በዜግነት ሃገርዎ (ሶሪያ፣ ኤርትራ፣ ኢራቅ፣ አፍጋኒስታን፣ ኢራን፣ ሊቢያ እና ሶማሊያ) የመሳሰሉ ምክንያቶችን ሊጨምር ይችላል።

አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ፣ ከ UNHCR ጋር በመመካከር፣ ከዚህ በታች የሚገኙትን የተወሰኑ የማመልከቻ ምድቦች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ማስታወቂያ አውጥቷል፡ http://www.ipo.gov.ie/en/ipo/pages/prioritisation_applicants

### መተው

በማመልከቻዎ ላይ በ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት እና በ የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት የጥበቃ ማመልከቻዎን ወይም ይግባኝዎን በማንኛውም ጊዜ መተው ይችላሉ። ማመልከቻዎን ከመተዎ በፊት ይህ የመተው ውሳኔ በእርስዎ እና በእርስዎ ጥገኝነት ስር ባሉ ሰዎች ላይ የሚያስከትለውን ውጤት ሙሉ በሙሉ ለመረዳት የህግ ምክር መጠየቅዎ አስፈላጊ ነው። አንድ ጊዜ ማመልከቻዎን ከተዉት ምርመራው ይጠናቀቅና ሚኒስትሩ የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ንዑስ ጥበቃ ይከለክልዎታል።

## በፈቃደኝነት መመለስ

የነጠላ አሰራሩ በመከናወን ላይ ባለበት በማንኛውም ደረጃ ላይ በፈቃደኝነት ወደመጡበት ሃገር/አዘውትረው ወደሚኖሩበት ሃገር ለመመለስ ምርጫ አለዎት። በፈቃደኝነት ለመመለስ ከወሰኑ፣ ዓለም አቀፍ የፍልሰት ድርጅት (IOM) ለጉዞዎ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍን ጨምሮ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍና ምክሮችን ሊሰጥዎ ይችላል። በተጨማሪም የ INIS በፈቃደኝነት የመመለስ ክፍልም እንዲሁ እገዛ ሊያደርግልዎት ይችላል።

በሂደቱ ውስጥ በፈቃደኝነት መመለስን ለማመቻቸት አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ዘንድ ያቀረቡትን የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ወይም የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ዘንድ ያቀረቡትን ይግባኝ መተው አለብዎት። በተጨማሪም በሂደቱ ማጠናቀቂያ ላይ በአየርላንድ ውስጥ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ከተከለከሉ እና የመቆየት ፈቃድ ካልተሰጠዎት፣ ሚኒስትሩ በፈቃደኝነት ወደመጡበት ሃገር/ አዘውትረው ወደሚኖሩበት ሃገር እንዲመለሱ የሚቻልባቸውን ሁኔታዎች ሊያሳውቅዎ ይችላል። የበለጠ ለማወቅ እባክዎ ይህንን ድረ ገጽ ይመልከቱ፡- **https://www.youtube.com/watch?v=eX7GarY2rUE**

## የአውሮፓ ህብረት የደብሊን ደንብ

የአውሮፓ ህብረት የደብሊን ደንብ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ለመመርመር የትኛው አባል ሃገር ሃላፊነት እንዳለበት የሚወስን የሕግ ሰነድ ነው። ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ሲያቀርቡ፣ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የአውሮፓ ህብረት የደብሊን ደንብን የተመለከተ የመረጃ መጽሃፍ ይሰጥዎታል። ቤተሰቦችዎ በሌላ የአውሮፓ ህብረት አባል ሃገር ውስጥ ሊኖሩ መቻላቸውን ጨምሮ ሌሎች የእርስዎን ማመልከቻ ለማየት ኃላፊነት ያለበት ሌላ አባል ሃገር መኖሩን የመሳሰሉ ምክንያቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ይህንን የመረጃ መጽሃፍ በጥንቃቄ ማንበብዎ ጠቃሚ ነው። ማመልከቻዎ በአውሮፓ ህብረት የደብሊን ደንብ ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ፣ ለእርስዎ የግል ጉዳይ የሚመለከቱ የደብሊን አሰራሮች እና እንደምታዎቹ ላይ ሌላ የመረጃ መጽሃፍ ይሰጥዎታል።

## ለዓለም አቀፍ ጥበቃ የሚቀርቡ ተከታይ ማመልከቻዎች

ስደተኝነት እና ንዑስ ጥበቃ ከተከለከሉ እና ማመልከቻዎ ከተዘጋ፣ አየርላንድ ውስጥ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ለማግኘት ሁለተኛ ወይም ተጨማሪ ማመልከቻ ለማቅረብ ከፈለጉ የሚኒስትሩ ፈቃድ ያስፈልግዎታል። ለተከታይ ማመልከቻ የሚኒስትሩን ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻዎን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላሉ። ከግምት ውስጥ የሚገቡ ሁኔታዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

ሀ. ካለፈው ማመልከቻ በኋላ አሁን ለዓለም አቀፍ ጥበቃ በጉልህ ብቁ እንዲሆኑ የሚያደርግዎት አዲስ መረጃ ከተገኘ እና ባለፈው ማመልከቻ ወቅት በመጀመሪያ ደረጃዎች ላይ መረጃውን ለማቅረብ ሳይችሉ ቀርተው የነበረ ከሆነ።

ለ. ያለፈው ማመለከቻዎ እርስዎ፣ የእርስዎ ጥፋት ባልሆነ ጉዳይ፣ ያለፈውን ማመልከቻዎን ለመቀጠል ሳይችሉ ቀርተው የተተወ ከሆነ ወይም እንደተተወ ከተቆጠረ።

ሚኒስትሩ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ተከታይ ማመልከቻ እንዲያቀርቡ ካልፈቀደልዎት፣ የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ዘንድ ቀርበው ይግባኝ ሊጠይቁበት የሚችሉት በምክንያት የተደገፈ ውሳኔ ይሰጥዎታል።

## የዳኝነት በድጋሚ መታየት

የዳኝነት በድጋሚ መታየት አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ እና የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎትን ጨምሮ የአስተዳደር አካላት እና ጉባዔዎች ውሳኔዎችን በአግባቡ እና በሕጉ መሰረት መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቆጣጠርበት መንገድ ነው። የዳኝነት በድጋሚ መታየት ይግባኝ አይደለም። በአየርላንድ የአስተዳደር ሕግ መሰረት አመልካቹ/ቿ፣ ከአማካሪው/ዋ ጋር በመተባበር የ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ እና/ወይም የ የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ውሳኔ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳግኝነት በድጋሚ እንዲታይ መጠየቅ ይችላል፣ ለምሳሌ ማመልከቻቸውን በተመለከተ በውሳኔ ሂደቱ ላይ የሕግ ስህተት ካለ። ለእርስዎ ማመልከቻ ተፈጻሚነት ያለው ስለመሆኑ አማካሪዎ ያማክርዎታል። ዳኝነትን በድጋሚ በማየት ላይ ያለ ፍርድ ቤት ዓለም አቀፍ ጥበቃን በተመለከተ አወንታዊ ምክረ ሃሳብ መስጠት እንደማይችል ነገር ግን አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ወይም የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት የፍርድ ቤቱን የሕግ ግኝት ከግምት ውስጥ በማስገባት አዲስ ውሳኔ እንዲሰጡ ሊጠይቅ እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል። ዳኝነትን በደጋሚ የማየት አሰራር በፍትህ እና እኩልነት ሚኒስትር ላይም ሊወሰድ ይችላል። በእርስዎ ጉዳይ ላይ ከእነዚህ አማራጮች መካከል አንደኛው ሊታሰብበት የሚገባ መሆኑን ለመወሰን እባክዎ ከአማካሪዎ ጋር ይነጋገሩ።

## በእስር መቆየት

አየርላንድ ውስጥ በሚከናወነው የጥበቃ አሰራር ወቅት አመልካቾች በእስር አይቆዩም። ነገር ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች አመልካቹ ምክንያታዊ በሆነ ደረጃ በሚከተሉት ጉዳዮች ከተጠረጠረ በፍልሰት ስራ መኮንን ወይም ጋርዳ ሲዮቻና (ፖሊስ) ያለ ማዘዣ ሊታሰር ይችላል፡-

I. በግዛቱ ውስጥ ለህዝብ ደህንነት ወይም ስነ-ስርዓት አደጋ የሚጥል ከሆነ፤

II. ከአየርላንድ ውጪ ከባድ ፖለቲካዊ ያልሆነ ወንጀል የፈጸመ ከሆነ፤

III. ማንነቱን ወይም ማንነቷን ለመግለጽ ምክንያታዊ የሆኑ ጥረቶችን ካላደረገ/ች፤

IV. አየርላንድን ለመቀቅ እና ያለምንም ሕጋዊ ፈቃድ ወደ ሌላ ሃገር ለመግባት ካሰበ፤

V. ለሰዎች በግዛቱ ውስጥ ዓለም አቀፍ ጥበቃ የመስጠት ስርዓቱን ወይም ከጋራ የጉዞ አካባቢ ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ስርዓቶች በሚያስተጓጉል መንገድ ከተንቀሳቀሰ ወይም የመንቀሳቀስ ሃሳብ ካለው፤ ወይም

VI. ያለምንም ተቀባይነት ያለው ምክንያት፣ የማንነት ማረጋገጫ ወይም የጉዞ ሰነዱን ወይም ሰነዷን ካወደሙ፣ ወይም ሃሰተኛ፣ የተቀየረ ወይም ምትክ የማንነት ማረጋገጫ ሰነድ ይዘው ከተገኙ።

በእነዚህ ሁኔታዎች የታሰረ አመልካች በህጉ ውስጥ ለዚህ ዓላማ በተዘጋጁ ቦታዎች ላይ በእስር ላይ ይቆያል። በዚህ ሕግ መሰረት ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች በእስር ላይ ሊቆዩ አይችሉም።

**በፖሊስ ጥበቃ ውስጥ ወይም በእስር ላይ ካለሁ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት እችላለሁ?**

በጥበቃ ወይም በእስር ላይ ከሆኑ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከት ይችላሉ። ለታሰሩበት የእስር ቤት አስተዳዳሪ ወይም የፖሊስ ጣቢያ ጋርዳ በተቻለ ፍጥነት ውስጥ ማመልከት እንደሚፈልጉ ማሳወቅ አለብዎ። ማመልከቻዎ እየተመረመረ ባለበት ወቅት በእስር ላይ ከቆዩ ቅድሚያ ይሰጥዎታል።

**የእስር ቆይታዬ በፍርድ ቤት ይታያል?**

ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች የተነሳ በእስር ላይ እንዲቆዩ የተደረጉ ከሆነ፣ በተቻለ ፍጥነት በታሰሩበት አካባቢ ውስጥ ከሚገኝ የዲስትሪክት ፍርድ ቤት ዳኛ ፊት ይቀርባሉ። በጉዳይዎ የተለየ ሁኔታ መሰረት የፍርድ ቤቱ ዳኛ የእስራት አጠቃቀሙን ይገመግማል።

# 5 የዓለም አቀፍ ጥበቃ ተጠቃሚዎች፡-

### የዓለም አቀፍ ጥበቃ ተጠቃሚ እንደመሆኔ የሚኖሩኝ መብቶች

የስደተኝነት ሁኔታ ወይም የንዑስ ጥበቃ ውሳኔ ካገኙ፣ የሚከተሉት መብቶች ይኖርዎታል፡-

- ከ3 ዓመት ላላነሰ ነገር ግን ለተወሰነ ጊዜ አየርላንድ ውስጥ የመኖር መብት፤
- ስራ መፈለግ እና መቀጠር፣ በማንኛውም ቢዝነስ፣ ንግድ ወይም ሙያ ላይ መሰማራት፤
- የአየርላንድ ዜጎች ካላቸው መብት ጋር ተመሳሳይ የሆነ የትምህርት እና ስልጠና መብት፤
- የአየርላንድ ዜጎች ከሚቀበሉት የሕክምና እና የማህበራዊ ዋስትና ጥቅማጥቀሞች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ጥቅማጥቅሞችን መቀበል፤
- የአየርላንድ ዜጎች ካላቸው መብት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ወደ አየርላንድ እና ከአየርላንድ የሚደረጉ የጉዞ መብቶች (ነገር ግን ሌላ ሃገር ለመግባት አሁንም ቢሆን ቪዛ የሚያስፈልግዎ መሆኑን ልብ ይበሉ፤
- የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ንዑስ ጥበቃ ከተሰጠዎት በኋላ ባለው አንድ ዓመት ውስጥ የተወሰኑ የቤተሰብዎ አባላት አየርላንድ እንዲገቡ እና መኖር እንዲችሉ ሚኒስትሩ ዘንድ ያመልክቱ።

### ለጉዞ ሰነድ እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት የጉዞ ሰነድ ለማግኘት ሚኒስትሩ ዘንድ ማመልከት ይችላሉ። የ80 ዩሮ ክፍያ መፈጸም አለብዎት። የጉዞ ሰነድ ለማግኘት ማመልከቻ ያቀረበው ሰው ማመልከቻውን ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ካላቀረበ፣ ለዚህ ማመልከቻ ያቀረበው ሰው ንዑስ ጥበቃ ያለው ከሆነ እና አገራዊ ፓስፖርት ማግኘት የሚችል ከሆነ፣ ወይም ሚኒስትሩ የጉዞ ሰነዱን መስጠት ለብሔራዊ ደህንነት፣ ለህዝባዊ ደህንነት፣ ለህዝብ ጤና ወይም ለህዝባዊ ስርዓት አደጋ የሚጥል ከሆነ ወይም ከህዝባዊ ፖሊሲ ጋር የሚቃረን ከሆነ ሚኒስትሩ የጉዞ ሰነድ አይሰጥም።

### የመቆየት ፈቃድ አለኝ። የጉዞ ሰነድ ለማግኘት ማመልከት እችላለሁ?

የስደተኝነት ወይም የንዑስ ጥበቃ ሁኔታ ካልተፈቀደልዎት ነገር ግን አየርላንድ ውስጥ የመቆየት ፈቃድ ከተሰጠዎት ከአገርዎ ኤምባሲ ፓስፖርት ለመጠየቅ ማመልከት አለብዎ። በአንዳንድ ልዩ ጉዳዮች፣ የመቆየት ፈቃድ የተሰጣቸው እና ፓስፖርት የሌላቸው ሰዎች በፍትሕ እና እኩልነት ሚኒስትር አማራጭ የጉዞ ሰነድ ሊሰጣቸው ይችላል።

የስደተኞች እና የንዑስ ጥበቃ ተጠቃሚዎች መብት በስፋት ሲታይ ተመሳሳይ ቢሆንም፣ እንደ ስደተኛ የስደተኛ የጉዞ ሰነድ የማግኘት መብት ይኖርዎታል። የንዑስ ጥበቃ ተጠቃሚ ከ INIS የጉዞ ሰነድ የሚያገኘው ከመጣበት ሃገር አገራዊ ፓስፖርት ለማግኘት ካልቻለ ብቻ ነው። የስደተኝነት ሁኔታ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የ1951 ኮንቬንሽን እና በፕሮቶኮሎቹ ውስጥም ዕውቅና የተሰጠው አቋም ነው። በተጨማሪም ስደተኞች ከሶስት ዓመት በኋላ የአየርላንድ ዜግነት እንዲሰጣቸው ማመልከት ሲችሉ፣ የንዑስ ጥበቃ ተጠቃሚዎች ግን አምስት አመት መጠበቅ አለባቸው።

የስደተኝነት ሁኔታ እና ንዑስ ጥበቃ ከተከለከሉ ነገር ግን የመቆየት ፈቃድ ከተሰጠዎት፣ ይህ ፈቃድ በ2004 የፍልሰት ሕግ ክፍል 4 መሰረት የሚሆን ነው። የሚሰጠው ፈቃድ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል። ይህም ፈቃዱ የተሰጠበትን የጊዜ ርዝመት እና ስራ ለመቀጠር፣ በንግድ ስራ ወይም ሙያ ላይ ለመሰማራት መፍቀድ አለመፍቀዱን ይጨምራል። የመቆየት ፈቃድ ጊዜው ሲያበቃ ሊታደስ ይችላል ነገር ግን በውስጡ የሚቀመጠው ጊዜ ርዝመት እና ሁኔታዎች በማንኛውም ጊዜ ሊከለሱ ይችላሉ።

የመቆየት መብት የተሰጠው ሰው በዓለም አቀፍ ሕግ መሰረት ከቤተሰብ ጋር ዳግም የመገናኘት መብት የለውም። ከቤተሰብ ጋር ዳግም ለመገናኘት ሊያመለክት የሚችለው በመደበኛ የኢሚግሬሽን አሰራር ሲሆን የተለዩ መስፈርቶች እና እሳቤዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ከቤተሰብ ጋር ዳግም መገናኘት

የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ንዑስ ጥበቃ ውሳኔ ከተሰጠዎት፣ ያንን ውሳኔ በተቀበሉ በ12 ወራት ውስጥ ከሚኒስትሩ ዘንድ የተወሰኑ የቤተሰብዎ አባላት ወደ አየርላንድ እንዲገቡ እና ከእርስዎ ጋር እንዲኖሩ፣ ወይም አስቀድመው አየርላንድ ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ደግሞ ከእርስዎ ጋር እንዲኖሩ እና እንዲቆዩ ማመልከት ይችላሉ።

በሚኒስትሩ የሚከናወን ምርመራን እና ውሳኔን ተከትሎ የቤተሰብ አባል ከ1 ዓመት ላላነሰ ጊዜ ከታደሰ ደግሞ ከ2 ዓመታት ላላነሰ የተወሰነ ጊዜ አየርላንድ ውስጥ ለመኖር ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል።

### ከቤተሰብ ጋር ዳግም መገናኘት ለሚለው ዓላማ የቤተሰብ አባል ተብሎ የተቀመጠው ማነው?

አዋቂ አመልካች ከሆኑ፣ የቤተሰብዎ አባላት በመባል የሚቀመጡት (i)የትዳር አጋርዎ ወይም የጉሮ አጋርዎ፣ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ በሚያመለክቱበት ጊዜ ጋብቻው ወይም የጉሮ አጋርነቱ ተመስርቶ የነበረ ከሆነ፤(ii)ልጅዎ፣ ከ18 ዓመት በታች እስከሆኑ ድረስ እና ለዓለም አቀፍ ጥበቃ በሚያመለክቱበት ወቅት ያላገቡ የነበረ ከሆነ።

### አብሮኝ ወላጅ የሌለ ልጅ ነኝ። ከቤተሰብ ጋር ዳግም ለመገናኘት አላማ ሲባል ለእኔ የቤተሰብ አባል ተብሎ የተቀመጠው ማነው?

ወላጆችዎ እና ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ እና ያላገቡ እህትና ወንድሞችዎ ቤተሰብዎ የሚወሰነው ይህንን ማመልከቻ ባቀረቡበት ጊዜ በነበረው መሰረት ነው።

### ከቤተሰብ ጋር ዳግም ለመገናኘት እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ንዑስ ጥበቃ ከተሰጠዎት፣ ለቤተሰብ ዳግም መገናኘት ክፍል፣ የአየርላንድ የዜግነት እና ፍልሰት ጉዳዮች አገልግሎት (Family Reunification Unit, the Irish Naturalisation and Immigration Service, 13/14 Burgh Quay, Dublin 2) በጽሁፍ ማመልከት ይችላሉ።

## ከቤተሰብ ጋር ዳግም ለመገናኘት የሚቀርብ ማመልከቻ አሰራር

የስደተኝነት ሁኔታ ወይም የንዑስ ጥበቃ ውሳኔዎን ከሚኒስትሩ ባገኙ በ12 ወራት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር ዳግም ለመገናነት ማመልከት አለብዎ። ለምሳሌ ማርች 1/2017 ላይ የስደተኝነት ሁኔታ ውሳኔ ቢሰጥዎት፣ ከማርች 1/2018 በፊት ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘት ማመልከት አለብዎት።

በጽሁፍ ለቤተሰብ ዳግም መገናኘት ክፍል፣ INIS ማመልከት እና የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ አለብዎ፦

- ስምዎን፣ የግል መታወቂያ ቁጥርዎን እነ አድራሻዎን፤
- ከሚኒስትሩ የስደተኝነት ሁኔታ ወይም ንዑስ ጥበቃ ያገኙበትን ቀን፤
- ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል፦ ስማቸውን፣ ከርስዎ ጋር ያላቸውን ዝምድና፣ የትውልድ ቀናቸውን፣ ዜግነታቸውን እና ወቅታዊ አድራሻቸውን።

በመልዕክት ልውውጡ ላይ የስደተኝነት ሁኔታዎን ወይም የንዑስ ጥበቃ ሁኔታዎን ውሳኔ ቅጂ ማያያዝዎም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ይህንን ማመልከቻ ተከትሎ ከቤተሰብ ዳግም መገናኘት ክፍል የሚሞላ መጠይቅ ይደርስዎታል። በዚህ ደረጃ፣ የቤተሰብዎን አባላት የተመለከቱ ዋና ሰነዶችንም እንዲያቀርቡ ሊጠየቁ ይችላሉ፣ ለምሳሌ የልደት ምስክር ወረቀቶች፣ አገራዊ መታወቂያ ካርዶች እና ፓስፖርቶች በቅርብ ጊዜ ከተነሱ ሁለት የፓስፖርት ከለር ፎቶዎች ጋር። በተጨማሪም የጉዞ ሰነድዎን ወይም ወቅታዊ አድራሻዎን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሊጠየቁም ይችላሉ። በግል ሁኔታዎ መሰረት፣ ከቤተሰብ ጋር ዳግም መገናኘት የሚጠይቁት ለባል ወይም ለሚስት ከሆነ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ወይም ሌሎች አግባብ የሆኑ መረጃዎችን ወይም የሰነድ ማስረጃዎችን እንዲያመጡ ሊጠየቁ ይችላሉ።

መጠይቅዎን ሞልተው ካቀረቡ በኋላ፣ የቤተሰብ ዳግም መገኛኘት ክፍል ማመልከቻዎን ይመረምርና የውሳኔ ደብዳቤ ይደርስዎታል። ከቤተሰብ ጋር ዳግም ለመገናኘት ከተፈቀደልዎት፣ ፈቃድ መሰጠቱን፣ የቤተሰብዎ አባላት መቼ መግባት እና/ወይም በግዛቱ ውስጥ መኖር መጀመር እንዳለባቸው የሚገልጽ የውሳኔ ደብዳቤ ይደርስዎታል። ጉዞዋቸውን ከዚያን ቀን በፊት ማመቻቸትዎ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም የቤተሰብዎ አባላት ከዚያ ቀን በፊት ወይም በዚያን ቀን አየርላንድ ካልገቡ፣ ከቤተሰብ ጋር የመገናኘት ፈቃዱ በስራ ላይ መዋሉ ያበቃል።

### አየርላንድ ውስጥ የቤተሰቤን አባል ለመቀላቀል በቅርቡ የተፈቀደልኝ የቤተሰብ አባል ነኝ። ያሉኝ መብቶች ምን ምንድናቸው?

ከአንድ አመት ላላነሰ ጊዜ፣ ከታደሰ ደግሞ ከሁለት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አየርላንድ ለመግባት እና/ወይም ለመኖር ፈቃድ አለዎት። የቤተሰብ አባል እንደመሆንዎ ያመጣዎት ሰው ያለው ዓለም አቀፍ ጥበቃ በስራ ላይ እስከሆነ ድረስ እና በግዛቱ ውስጥ ነዋሪ እስከሆኑ ድረስ ያመጣዎት ሰው ካሉት መብቶች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መብቶች አለዎት።

# 6 መሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

አንዳንድ ሰዎች የዓለም አቀፍ ጥበቃ ሕግ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 31/2016 ላይ ስራ ከመጀመሩ በፊት ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ አቅርበው ሊሆን ይችላል። ለስደተኝነት ሁኔታ እና ንዑስ ጥበቃ ያቀረቧቸውን ማመልከቻቸ ከስደተኞች ማመልከቻ ኮሚሽነር (ORAC) እና የተወሰኑ ይግባኞችን ደግሞ ከስደተኞች ይግባኞች ጉባዔ (RAT) ወደ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ለማዘዋወር አንዳንድ ማመቻቻዎች በስራ ላይ ውለዋል። እነዚህ አመልካቾች የማመልከቻቸውን የሽግግር ሁኔታዎች አስመልክቶ ከ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የማብራሪያ ደብዳቤ ሊደርሳቸው ይገባል።

ከዚህ በታች የሚገኙት ስዕላዊ መግለጫዎች ወደ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የተላለፉ ጉዳዮችን ዋና ዋና ፈርጆች ያስቀምጣሉ። በስተግራ በኩል ያሉት ሳጥኖች ከዲሴምበር31 2016 በፊት የተደረጉ ማመልከቻዎችን የሚያመላክቱ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። በሽግግር ሁኔታዎች ላይ **አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የመረጃ ማስታወሻ ውስጥ የበለጠ መረጃ በዚህ ድረ ገጽ ላይ ይገኛል:-** http://ipo.gov.ie/en/IPO/Pages/Transitional_Arrangements ማመልከቻዎን በተመለከተ ተጨማሪ ምክር ከፈለጉ እባክዎ ጠበቃዎን ያማክሩ።

ከዲሴምበር 31/2016 በፊት ለ ORAC የስደተኝነት ሁኔታ ማመልከቻ አስገብቼ ነበር ነገር ግን በጉዳዩ ላይ ምክረ ሃሳብ አልደረሰኝም።

የዓለም አቀፍ ጥበቃ ፍላጎቶችዎን ለመመርመር መዝገብዎ ወደ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ይዘዋወራል። ይህም ማለት በነጠላ አሰራሩ ውስጥ አዲስ መጠይቅ ይሞላሉ እንዲሁም አዲስ ቃለ-መጠይቅ ይኖርዎታል ማለት ነው።

ለስደተኝነት ሁኔታ ያቀረብኩት ማመልከቻ፣ ከዲሴምበር 31/2016 በፊት RAT ዘንድ ይግባኝ ላይ ነበር ነገር ግን የጉባዔው ውሳኔ አልደረሰኝም

ለንዑስ ጥበቃ ብቻ ያለዎትን መብት ለመመዘን መዝገብዎ ወደ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ይዘዋወራል። እንዲሁም በንዑስ ጥበቃ ላይ ብቻ አዲስ መጠይቅ ይሞላሉ አዲስ ቃለ-መጠይቅም ይደረግልዎታል። አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ለንዑስ ጥበቃ ያቀረቡትን አቤቱታ ከተቃወመ ሚኒስትሩ የመቆየት ፈቃድ ሊሰጥዎ የሚችል መሆኑን ያጤናል። የንዑስ ጥበቃ ክልከላው ላይ ይግባኝ ካቀረቡ፣ ይግባኝዎ በተከለከሉት የስደተኝነት ሁኔታ ላይ የሚቀርብ ይግባኝንም ይጨምራል፣ ስለዚህ ሁለት ይግባኞች በጋራ ይታያሉ፣ ማለትም የስደተኝነት ሁኔታ እና የንዑስ ጥበቃ ሁኔታ።

ከዲሴምበር 31/2016 በፊት ለ ORAC የስደተኝነት ሁኔታ ማመልከቻ አስገብቼ ነበር ነገር ግን እስካሁን ድረስ በማመልከቻዬ ላይ ምርመራ መደረግ አልጀመረም።

ለንዑስ ጥበቃ ብቻ ያለዎትን መብት ለመመዘን መዝገብዎ ወደ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ይዘዋወራል። እንዲሁም በንዑስ ጥበቃ ላይ ብቻ አዲስ መጠይቅ ይሞላሉ አዲስ ቃለ-መጠይቅም ይደረግልዎታል። ORAC የሰጠው እና የስደተኝነት ሁኔታ የከለከለዎት ምክረ ሃሳብ እና የ RAT ውሳኔ (በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚ ከሆነ) በስራ ላይ ይቆያሉ። አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ለንዑስ ጥበቃ ያቀረቡትን አቤቱታ ከተቃወመ ሚኒስትሩ የመቆየት ፈቃድ ሊሰጥዎ የሚችል መሆኑን ያጤናል። በተጨማሪም አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የንዑስ ጥበቃ መብት ከከለከለዎት ለ የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።

**ለንዑስ ጥበቃ ያቀረብኩት ማመልከቻ ከዲሴምበር 31/2016 በፊት RAT ዘንድ ነበር። ማመልከቻዬ ምን ይደረጋል?**

**RATን የተካው የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ለንዑስ ጥበቃ ብቻ የይግባኝ ውሳኔ ይሰጣል። ከዚህ በማስከተል በ1999 የፍልሰት ሕግ ክፍል 3 ስር ለተቀመጠው "የመቆየት ፈቃድ (leave to remain)" የፍትህ እና እኩልነት ሚኒስትር ዘንድ በጽሁፍ ማመልከቻ እንዲያቀርቡ መብት ይሰጥዎታል። ለእነዚህ ውሳኔዎች መነሻ የሚሆኑት ነጥቦች በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ በ2015 ዓለም አቀፍ ጥበቃ ህግ ላይ "የመቆየት ፈቃድ" ከተቀመጡት እሳቤዎች ይለያሉ። ለበለጠ መረጃ እባክዎ ከሕጋዊ ወኪልዎ ጋር ይነጋገሩ።**

**ከዲሴምበር 31/2016 በፊት በደብሊን ደንብ ላይ ለ RAT ይግባኝ አቅርቤያለሁ። ማመልከቻዬ ምን ይደረጋል?**

**RATን የተካው የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት በደብሊን ደንብ ውሳኔ ላይ ለሚቀርብ ይግባኝ ብቻ ውሳኔ ይሰጣል። ይግባኝዎ ተቀባይነትን ካገኘ፣ ማመልከቻዎ አየርላንድ ውስጥ በመደበኛው አሰራር በኩል ይታያል።**

# 7 በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች፡-

**ጥ.** ዓለም አቀፍ ጥበቃ ምንድነው?

**መ.** ዓለም አቀፍ ጥበቃ በአውሮፓ ህብረት ሕግ ውስጥ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ የሚውል ሃረግ ሲሆን፣ የስደተኝነት እና የንዑስ ጥበቃ ሁኔታዎችን ይወክላል። አየርላንድ ውስጥ ጥገኝነት የሚጠይቁ ሰዎች በትውልድ ሃገራቸው ውስጥ ከሚደርስባቸው እስራት ወይም ከባድ ጉዳት ዓለም አቀፍ ከለላ የሚፈልጉ ናቸው።

**ጥ.** ስደተኛ ማነው?

**መ.** ስደተኛ ማለት በዘር፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ የተወሰነ ማህበረሰብ ቡድን አባል በመሆን ወይም በፖለቲካ አመለካከት ምክንያት እስራትን ለመሸሽ አጥጋቢ ምክንያት ያለው እና ወደ ሃገሩ ሊመለስ ያልቻለ ሰው ነው።

የስደተኝነት ሁኔታ፣ የስደተኝነትን ትርጓሜ ለሚያሟሉ ሰዎች የሚሰጥ የጥበቃ አይነት ነው።

**ጥ.** ንዑስ ጥበቃ ምንድነው?

**መ.** ንዑስ ጥበቃ ከስደተኝነት ሁኔታ ጋር አብሮ የሚመጣ ነው። ይህም ማለት አንድ ሰው ከባድ ጉዳት ይገጥመኛል ብሎ በመፍራት ወደ ትውልድ ሃገሩ ወይም አዘውትሮ ወደሚኖርበት ሃገር መመለስ አይችልም ማለት ነው። ከባድ ጉዳት ማለት (i) የሞት ቅጣት

ወይም ፍርድ፤ (ii)ስቃይ ወይም ኢሰብአዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት፤ (iii) በዓለም አቀፍ እና የውስጥ ጦርነት ሁኔታዎች ውስጥ በማዳለት በሚደረግ ጥቃት የተነሳ በግለሰብ ህይወት ላይ ከባድ እና የተነጣጠረ አደጋ።

ጥ. የመቆየት ፈቃድ ምንድነው?

መ. የመቆየት ፈቃድ የሚመረመረው ለስደተኝነት ሁኔታ ወይም ለንዑስ ጥበቃ መብት የሌለዎት ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው። ይህ የእርስዎን ቤተሰባዊ ወይም የግል ሁኔታዎች የመሳሰሉ ሌሎች ምክንያቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሚኒስትሩ አየርላንድ ውስጥ ለመቆየት ፈቃድ ለመስጠት ወይም ላለመስጠት የሚያርገው እሳቤ ነው።

ሚኒስትሩ የሚከተሉትን የመሳሰሉ ምክንያቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባል፡-

ሀ. ከአየርላንድ ጋር ግንኙነት ካለዎት፣ የግንኙነትዎን ሁኔታ፤
ለ. ሰብዓዊ እሳቤዎች፤
ሐ. ማናቸውንም የወንጀል ጥፋቶችን ጨምሮ አየርላንድ ውስጥም ሆነ ውጪ ያለዎትን ባህርይ እና ስነ-ምግባር፤
መ. የጋራ ጥቅም እሳቤዎች።

ሚኒስትሩ የመቆየት ፈቃድን በሚያጤንበት ጊዜ ለእስራት ሊጋለጡ ወደሚችሉበት ሃገር ያለመላክ ክልከላንም ከግምት ውስጥ ያስገባል።

ጥ. ለእስራት ሊጋለጡ ወደሚችሉበት ሃገር ያለመላክ ክልከላ ማለት ምን ማለት ነው?

መ. ይህ መርሃ ማለት ሚኒስትሩ ማንኛውንም ሰው በማንኛውም ሁኔታ ወደ ግዛቱ ድንበር መመለስ አይችልም ይህ የሚሆነው በሚኒስትሩ አስተያየት (ሀ) የዛ ሰው ህይወት ወይም ነጻነት በዘር፣ በሃይማኖት የተወሰነ ማህበረሰብ ቡድን አባል በመሆን ወይም በፖለቲካ አስተያየቱ ምክንያት አደጋ ላይ ከወደቀ ወይም (ለ) ሰውየው ለሞት ቅጣት፣ ስቃይ ወይም ሌሎች ኢ-ሰብዓዊ ወይም ክብርን የሚነኩ አያያዞች ወይም ቅጣቶች የመጋለጥ ከባድ ስጋት ካለበት።

ጥ. "የመቆየት ፈቃድ (leave to remain)" ምንድነው?

መ. የመቆየት ፈቃድ (leave to remain) የ2015 ዓለም አቀፍ ጥበቃ ሕግ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በስራ ላይ የነበረ አሰራር ነው። የ1999 የፍልሰት ሕግ ክፍል 3 በመቆየት ፈቃድ (leave to remain) ላይ ውሳኔ ለመስጠት ሚኒስትሩ ከግምት የሚያስገባቸውን ሁኔታዎች ያስቀምጣል። በግዴታ ወደ ሃገራቸው እንዲመለሱ የተወሰነባቸውን ሰዎች እና ከዚህ ቀደም ለጥገኝነት ጠይቀው በማያውቁ ሰዎች ጉዳይ ላይን ጨምሮ ድንጋጌዎቹ ተፈጻሚ መሆናቸውን ይቀጥላሉ። አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ተሸጋጋሪ ጉዳዮች ብቻ (ከላይ ይመልከቱ) በእነዚህ አሰራሮች መሰረት መከናወናቸውን ይቀጥላሉ።

ጥ. በወላጅ የዓለም አቀፍ ጥበቃ አቤቱታ ላይ ጥገኛ መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

መ. ይህ ማለት ጥገኛ የሆነ ልጅ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ምዘና በወላጁ አቤቱታ ውስጥ ይጠቃለልና ውጤቱም በዚህኛው አቤቱታ ውጤት ላይ የተመሰረተ ይሆናል ማለት ነው። ጥገኛ የሆነው ልጅ የተለየ ቃለ-መጠይቅ አይደረግለትም ወይም የጥበቃ ፍላጎቶቹ በተለየ ምርመራ አይደረግባቸውም። ወላጅ ልጁ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ለምን እንደሚያስፈልገው እና/ወይም አየርላንድ ውስጥ የመቆየት ፈቃድ ለምን ሊሰጠው እንደሚገባ በማመልከቻው ሂደት ላይ ማናቸውንም ምክንያቶች ማካተት አለበት። ልጆች ከወላጆቻቸው በተጨማሪ ወይም በተለየ የጥበቃ ፍላጎቶች ሊኖሯቸው እንደሚችሉ ማስታወስ ያስፈልጋል።

ጥ. ዜግነት የሌለኝ ሰው ከሆንኩኝ አየርላንድ ውስጥ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ለማግኘት ማመልከቻ ማቅረብ እችላለሁ?

መ. አዎን፣ ዜግነት የሌለዎት ሰው ከሆኑ፣ አየርላንድ ውስጥ የስደተኝነት ሁኔታ እና ንዑስ ጥበቃ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። ከዚያ ማመልከቻዎ አዘውትረው ከሚኖሩበት ቦታ ጋር በተያያዘ ይመረመራል፣ ማለትም ከዚህ ቀደም ከኖሩት ሃገር አንጻር።

ጥ. አካል ጉዳት እና/ወይም ሌሎች የልዩ ፍላጎት ሁኔታዎች ያሉብኝ ከሆነስ?

መ. የሚቻል ከሆነ በግል ለሚደረግልዎት ቃለ-መጠይቅ አለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የሚያስፈልጉዎትን ነገሮች እንዲያመቻች ማንኛውንም አካል ጉዳት ወይም የልዩ ፍላጎት ሁኔታ ለ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ በተቻለ ፍጥነት ማሳወቅ አለብዎ።

**ጥ.** የተሰጠኝ ስደተኝነት ሁኔታ ውሳኔ ወይም የንዑስ ጥበቃ ውሳኔ ሊሻር ይችላል?

**መ.** አዎን፣ በአንዳንድ ውስን በሆኑ ሁኔታዎች የስደተኝነት ውሳኔ ወይም የንዑስ ጥበቃ ውሳኔ ሊሻር ይችላል፣ ለምሳሌ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ያቀረቡት ማመልከቻ በሚመረመርበት ጊዜ ሃሰተኛ ወይም አሳሳች መረጃ ሰጥተው ሲገኙ። ይህ ሲከሰት፣ ሚኒስትሩ ምክንያቶችን ጨምሮ ሁኔታዎን ለመሻር በጽሁፍ ሃሳቡን ይገልጽልዎታል። በምላሹም ለሚኒስትሩ ማሳወቂያው በደረሰዎት በ15 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ መልስ እንዲሰጡ ዕድል ይሰጥዎታል። ሚኒስትሩ ሁኔታዎን ለመሻር ከወሰነ፣ በ10 ቀናት ውስጥ ያንን ውሳኔ በመቃወም ለሰርኪዩት ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቅርቡ።

**ጥ.** በዓለም አቀፍ ጥበቃ አሰራሩ ወቅት የት እቆያለሁ?

**መ.** በቅበላ እና ቅንጅት ኤጀንሲ አማካኝነት በቀጥታ ቁጥጥር ማዕከል ውስጥ መኖሪያ ቦታ ይሰጥዎታል፣ ነገር ግን ራስዎን ለማኖር የሚያስችል የገንዘብ አቅም ካለዎት የፈለጉት ቦታ መኖር ይችላሉ። የቅበላ ሥርዓቱ የሚመራው በ2018ቱ የአውሮፓ ማህበረሰቦች (የቅበላ ሁኔታዎች) ደንብ ሕጋዊ ሰነዶች ቁ. 230/2018 ነው።

## በ1ኛ ሙከራ የስደተኝነት ሁኔታ መስጠት

### ለዓለም አቀፍ ጥበቃ የሚቀርብ ማመልከቻ

የ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ምርመራ እና ምክረ ሃሳብ

የስደተኝነት ሁኔታ ይመከራል

አመልካቹ ለግዛቱ ደህንት አደጋ ካልሆነ በስተቀር ሚኒስትሩ የስደተኝነት ሁኔታ ይሰጣል

## በ1ኛ ሙከራ ንዑስ ጥበቃ መስጠት

### ለዓለም አቀፍ ጥበቃ የሚቀርብ ማመልከቻ

የ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ ምርመራ እና ምክረ ሃሳብ

የስደተኝነት ሁኔታ ሳይሆን ንዑስ ጥበቃ ይመከራል

ሚኒስትሩ የንዑስ ጥበቃ ውሳኔ ይሰጣል

የስደተኝነት ሁኔታ ላይ ይግባኝ የሚጠየቀው የአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎትየአለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ልዩ ችሎት ዘንድ ብቻ ነው

ያልተሳካ ይግባኝ፡- የ SP ውሳኔ በስራ ላይ ይቆያል


የተሳካ ይግባኝ

አመልካቹ ለግዛቱ ደህንት አደጋ ካልሆነ በስተቀር ሚኒስትሩ የስደተኝነት ሁኔታ ይሰጣል። የንዑስ ጥበቃ ውሳኔ ስራ ላይ መዋሉ ያበቃል

## በ1ኛ ሙከራ የመቆየት መብት መስጠት



# በ1ኛ ሙከራ የስደተኝነት ሁኔታ፣ ንዑስ ጥበቃ እና የመቆየት ፈቃድ መከልከል



# 8 አግባብ የሆኑ ድርጅቶች እና አካላት የአድራሻ ዝርዝር

**ይህንን የመረጃ መጽሃፍ ካነበቡ በኋላም አዲሱን ነጠላ አሰራር ወይም ዓለም አቀፍ ጥበቃ ሕግ በሚመለከት ጥያቄ አለዎት?**

ቢሯችን ማነጋገር እና/ወይም አማካሪዎን መጠየቅ ይችላሉ።

**የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ የአየርላንድ የዜግነት መስጠት እና የፍልሰት አገልግሎት (International Protection Office Irish Naturalisation & Immigration Service)**
79-83 Lower Mount Street,
Dublin 2, D02 ND99
**ስልክ፡-** +353 1 602 8000
**ፋክስ፡-** +353 1 602 8122
**ኢሜይል፡-** ipo@justice.ie
**www.ipo.gov.ie**

**የዓለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኞች ጉባዔ (International Protection Appeals Tribunal)**
6/7 Hanover Street,
Dublin 2, D02 W320
**ስልክ፡-** +353 1 474 8400
**ቅናሽ ጥሪ፡-** 1890 210 458
**ፋክስ፡-** +353 1 474 8410
**ኢሜይል፡-** info@protectionappeals.ie
**www.protectionappeals.ie**

**የአየርላንድ ዜግነት መስጠት እና የፍልሰት አገልግሎት (Irish Naturalisation & Immigration Service)**
Department of Justice &
Equality 13-14 Burgh Quay,
Dublin 2, D02 XK70
**ስልክ፡-** +353 1 616 7700
**ቅናሽ ጥሪ፡-** 1890 551 500
**www.inis.gov.ie**

**የቅበላ እና ቅንጅት ኤጀንሲ (Reception and Integration Agency)**
P.O. Box 11487, Dublin 2
**ስልክ፡-** +353 1 418 3200
**ፋክስ፡-** +353 1 418 3271
**ኢሜይል፡-** RIA_Inbox@justice.ie
**www.ria.gov.ie**

**ዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (International Organisation for Migration)**
116 Lower Baggot Street,
Dublin 2, D02 R252
**ስልክ፡-** +353 1 676 0655
**ነጻ የስልክ መስመር፡-** 1800 406 406
**ኢሜይል፡-** iomdublin@iom.int
**www.ireland.iom.int**

**የሕግ ድጋፍ ቦርድ ደብሊን (Legal Aid Board Dublin)**
48/49 North Brunswick Street,
Georges Lane, Dublin 7
D07 PE0C
**ስልክ፡-** +353 1 646 9600
**ፋክስ፡-** +353 1 671 0200
**ኢሜይል፡-** lawcentresmithfield@legalaidboard.ie

**የሕግ ድጋፍ ቦርድ ጋልዌይ (Legal Aid Board Galway)**
9 Francis Street Galway,
H91 NS53
**ስልክ፡-** +353 91 561 650
**ፋክስ፡-** +353 91 563 825
**ኢሜይል፡-** galwaylawcentre@legalaidboard.ie

**የሕግ ድጋፍ ቦርድ ኮርክ (Legal Aid Board Cork)**
Popes Quay Law Centre,
North Quay House,
Popes Quay, Shandon,
Cork, T23 HV26
**ስልክ፡-** +353 21 4551 686
**ፋክስ፡-** +353 21 455 1690
**ኢሜይል፡-** lawcentrecorknorth@legalaidboard.ie

**ጥገኝነት የሚጠይቁ እና ከወላጆቻቸው የተለዩ ልጆች ቡድን (Team for Separated Children Seeking Asylum, Tusla – Child & Family Agency)**
Sir Patrick Dun's Hospital,
Lower Grand Canal Street,
Dublin 2, D02 P667
**ስልክ፡-** +353 1 647 7000
**ፋክስ፡-** +353 1 647 7008
**www.tusla.ie**

**Irish Refugee Council**
37 Killarney Street,
Mountjoy, Dublin 1
**ስልክ፡-** +353 1 764 854
**ፋክስ፡-** +353 1 672 5927
**ኢሜይል፡-** info@irishrefugeecouncil.ie
**www.irishrefugeecouncil.ie**

**Nasc Ireland**
Ferry Lane, Dominic Street, Cork
**ስልክ፡-** +353 21 450 3462
**ኢሜይል፡-** info@nascireland.org
**www.nascireland.org**

**Doras Luimni**
Central Buildings 51a,
O' Connell Street,
Limerick, V94 268W
**ስልክ፡-** +353 61 310 328
**ኢመይል፡-** info@dorasluimni.org
**www.dorasluimni.org**

**Crosscare Refugee Service**
2 Sackville Place, Dublin 1
**ስልክ፡-** +353 1 873 2844
**ፋክስ፡-** +353 1 872 7003
**ኢሜይል፡-** refugeeservice@crosscare.ie
**www.crosscare.ie**

**SPIRASI**
213 North Circular Road,
Phibsborough, Dublin 7
**ስልክ፡-** +353 1 838 9664
ወይም +353 1 868 3504
**ፋክስ፡-** +353 1 882 3547
**ኢሜይል፡-** info@spirasi.ie
**www.spirasi.ie**

**Jesuit Refugee Service Ireland**
The Mews, 20 Upper Gardiner St.
Dublin 1
**ስልክ፡-** +353 1 814 8644
**www.jrs.ie**

**UNHCR**
102 Pembroke Road,
Ballsbridge, Dublin 4,
Ireland
**ስልክ፡-** + 353 1 6314510
**ኢ-ሜይል፡-** iredu@unhcr.org
**www.unhcr.ie**

www.unhcr.ie

UNHCR
The UN Refugee Agency